SECURITY AND JUSTICE FOR TIGRAYANS (SJT)
ድሕንነትን ፍትሕን ንትግራዎት
907 T Street NW, Suite-Basement, Washington DC 20001

NOVEMBER 15, 2021

# ከትግራይ ተወላጆች ለመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ የቀረበ ጥሪ

## በሕዝብ ላይ የታወጀው የዘር ማጥፋት ጦርነት ለማስቆምና ለሰላም መታገል ለነገ የማይባል ኣስቸኳይ ጉዳይ ነው፤

ከሶስት ኣመት ገደማ በፊት ስልጣን ላይ ሲወጡ "ኢትዮጵያ ያለ ትግራይ ማለት መኪና ያለ ሞተር እንደማለት ነው" በማለት የተናገሩት ጠ/ሚኒስትር ኣብይ ኣሕመድ በትግራይ ሕዝብ ላይ ጦርነት ከከፈቱ ይኸው ከኣንድ ዓመት በላይ ሆኗቸዋል። በዚህ ከኣንድ ዓመት በላይ ባስቆጠረው ጦርነት የትግራይ ሕዝብ በታሪኩ ኣጋጥሞት የማያውቅና ለማመን በሚያስቸግር የጭካኔና የኣረመኔነት ደረጃ ጭፍጨፋና ግፍ እየተፈጸመበት ይገኛል። በኣጭሩ ለመጥቀስ ያህል፤

1. ከኣንድ ሺህ ኣምስት መቶ ዓመት በላይ ታሪክ ያላቸው ገዳማት በከባድ መሳርያ ተደብድበዋል፤ ተዘርፈዋል፤ መነኩሳት ተገድለዋል፤ ከገዳማቸው ተባረዋል፤ ተንገላተዋል። ቤተክርስትያናትና መስጊዶች ፈርሰዋል፤ ተዘርፈዋል። ካህናትና ዲያቆናት በቤትክርስትያን ግቢና ከዚያም ውጭ በመቶዎች የሚቆጠሩ ተግድለዋል። በቤተክርስትያን ለጸሎት የተገኙት ምእመናንና ከጦርነቱ በመሸሽ ለመጠለልና ህይወታቸውን ለማትረፍ በቤተክርስትያን ግቢ የተገኙ ሰላማዊ ሰዎች በግፍ ተጨፍጭፈዋል።
2. ሴቶች በቃላት ለመግለጽ በሚያጸይፍ ኣኳኋን ክብራቸው ተደፍረዋል። በሴትነታቸው እንዲያፍሩ፤ በቀጣይ ህይወታቸውም ቤተሰብ እንዳይመሰርቱና ልጅ እንዳይወልዱ ባቀደ መንገድ የኣራዊት ስራ ተፈጽሞባቸዋል። ከወጣት እስከ ኣዛውንት በቤተሰቦቻቸው ፊት ተደፍረዋል። ይህ ሁሉ ግፍ ከተፈጸመባቸው በኋላም ህክምና እንዳያገኙና ሆን ተብሎ ለተለያዩ በሽታዎች እንዲጋለጡ ተደርገዋል። የዚህ ግፍ ሰለባ የሆኑት ሴቶች ቁጥር በውል ለማወቅ ብዙ ጊዜና ጥረት የሚጠይቅ ቢሆንም እስካሁን ከሚቀርቡ መረጃዎች ከሃያ ሺህ በላይ የሚሆኑ በተለያየ የእድሜ እርከን የሚገኙ ሴቶች ዘግናኝና ኣጸያፊ በሆነ መንገድ ተደፍረዋል።
3. ንጹሃን ዜጎች በጅምላ ተጨፍጭፈዋል። ወጣቶች እንደ ከብት ታርደው ወደ ገደል ተወርውረዋል፤ ወደ ወንዝ ተጥለዋል፤ በወላጆቻቸው ፊት ተገድለዋል።
4. የሰላማዊ ሰዎች የቤት ንብረትና ያፈሩት እህል ተዘርፏል፤ እርሻቸው ተቃጥሏል፤ ከብቶቻቸው ታርደዋል፤ ተገድለዋል፤የእርሻ መሳርያዎቻቸው ተነጥቀዋል። ከመሬታቸውና ከቤት ንብረታቸው ተፈናቅለው ለስደትና ለእንግልት ተዳርገዋል። የትግራይ ከተሞች በኣሁኑ ጊዜ ከተለያዩ ቦታዎች በተለይም ደግሞ ከምዕራብ ትግራይ በመጡ ተፈናቃዮችና እርዳታ ፈላጊዎች ተጨናንቀዋል።
5. ፋብሪካዎችና የንግድ ድርጅቶች ተዘርፈዋል፤ ከዝርፍያ የቀረውም እንዲወድም ተደርጓል። የትግራይ ኢኮኖሚ እንዳልነበረ ሆኖ ደቋል። የመንግስትም ሆነ የግል ድርጅት ሰራተኞች ተበትነዋል። ከዚህም የተነሳ በኣሁኑ ጊዜ ከ90 በመቶ በላይ የትግራይ ህዝብ እርዳታ ፈላጊ እንዲሆን በመዳረጉ እናቶች፤ ህጻናትና፤ ሽማግሌዎች በየቀኑ በረሃብ እየረገፉ ይገኛሉ።
6. የትግራይ ህዝብ የህክምናም ሆነ የትምህርት ኣገልግሎት እንዳያገኝ የህክምና መገልገያና የትምህርት ተቋማት ተዘርፈዋል፤ ወድመዋል፤ የህክምናና የትምህርት ባለሙያዎች እንዲበታተኑ ሆነዋል። የባንክ፤ የስልክና የኢንተርነት፤ የመብራት፤ የመጓጓዣ ኣገልግሎት፤ እና የተለያዩ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ኣግልግሎቶች ተዘግተውባቸዋል። በባንክ ያጠራቀሙት ገንዘብ እንዳይጠቀሙ፤ ከኣገር ውስጥም ሆነ ከኣገር ውጭ ምንም ዓይነት ገንዘብ እንዳይደርሳቸው በማድረግ የትግራይ ኢኮኖሚ ሙሉ በሙሉ እንዲዘጋ ተደርጓል።
7. በኣጠቃላይ ትግራይን ከሌላው የኢትዮጵያ ክፍልም ሆነ ከውጭው ዓለም በማንኛውም መንገድ እንዳይገናኝ በማድረግና በከበባ ስር በማስገባት የትግራይ ህዝብ በኣየርና በመሬት በሚደረገው ጦርነት ለመጨርስና ከጦርነቱ የተረፈም በረሃብና በበሽታ እንዲያልቅ ከተፈርደበት ይኸው ድፍን ኣንድ ዓመት ሆኖታል።
8. በዚህ የትግራይ ህዝብን እንደህዝብ ለማጥፋት እየተካሄደ ባለው ጦርነት በኣዝማችነት እየመራ ያለው ራሱ የኢትዮጵያ መንግስት መሆኑ ከሰብኣዊነትም ሆነ ከኣገራዊ ማንነት ኣኳያ ሲታይ በጣም የሚያሳዝንና የኢትዮጵያን ማህበራዊ፤ ኢኮኖሚያዊና፤ ፖሊቲካዊ ተጋምዶን (social, economic, and political fabrics) የሚያጠፋ ነው። ይባስ ብሎ ደግሞ የትግራይን ሕዝብ ለማጥፋት የኢትዮጵያ መንግስት የራሱ ሃይል ኣልበቃ ብሎት የኤርትራና የሌሎች ባእድ ኣግሮች ወታደሮች በትግራይ ውስጥ ገብተው የትግራይ ህዝብንና ማንነቱን ለማጥፋት ማመን በሚከብድ ደረጃ የጥፋት ድግስ እንዲደግሱበት ማድረጉ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ምን ጊዜም የማይረሳ ጥቁር ጠባሳ ሆኖ ይኖራል።
9. ከትግራይ ውጭ በተለያዩ የኢትዮጵያ ክልሎች የሚገኙ የትግራይ ተወላጆች ላይ እየደረሰ ያለውም በተመሳሳይ ለማመን በሚያስቸግር ደረጃ ማሰር፤ ማሳደድና ግድያ እየተፈጸመባቸው ይገኛል፤ በኣዲስ ኣበባ ከተማ በተለያየ የመንግስትና የግል ስራ በሚተዳደሩ የትግራይ ተወላጆች ላይ እየደረሰ ያለው ጥቃትና እንግልት ለማመን ያስቸግራል። በተለያዩ የመንግስት መንግስት መስሪያ ቤቶችና ድርጅቶች በመስራት ላይ የነበሩት የትግራይ ተወላጆች በማንነታቸው ብቻ እየታደኑ ከስራ እንዲባረሩ፤ ታፍነው እንዲወሰዱና፤ እንዲታሰሩ እየተደረገ ነው።

    - በሺዎች የሚቆጠሩ የትግራይ ተወላጆች የንግድና የስራ ድርጅቶች ተዘግተዋል፤ ሰራተኞቻቸው ተበትነዋል፤ ባለቤቶቻቸውም ለእስርና ለእንግልት ተዳርገዋል።
    - በኦርቶዶክስና በካቶሊክ ቤተ ክርስትያናት በተለያየ ሃላፊነት በማገልገል ላይ ያሉ የትግራይ ተወላጅ ቀሳውስት፤ ካህናትና፤ ዲያቆናት ያለምንም ምክንያት ታፍሰው ለእስርና ለስቃይ ተዳርገዋል። በኣዲስ ኣበባ ብቻ እስካሁን ድረስ ከኦርቶዶስ ቤተ

ክርስትያን ከተለያዩ ኣድባራት ከ100 በላይ ካህናትና ዲያቆናት፤ ከካቶሊክ ቤተ ክርስትያን ከ30 በላይ ካህናት ታፍሰው ታስረዋል። ቁጥራቸው በውል ያልታወቀ የትግራይ ተወላጅ የሆኑ የእስልምና መሪዎትም ታፍሰዋል።

- በተባበሩት መንግስታት ልዩ ልዩ ድርጅቶችና በሌሎች ዓለም ኣቀፍ ድርጅቶች ሲሰሩ የነበሩ የትግራይ ተወላጆች በማንነታቸው ምንክንያት በመንግስት ጫና ከስራቸው እንዲባረሩና እንዲታሰሩ እየተደረገ ይገኛል።

10. ከኣዲስ ኣበባ ውጭ በሚዛን ቴፒ፤ በደብረብርሃን ከተማ፤ ሃዋሳና ዲላ ኣከባቢ፤ ኣዋሽ ኣከባቢ በትግራይ ተወላጆች ላይ ከፍተኛ የማዋከብ ስራ እየተሰራ ይገኛል፤ እነዚህ ለምሳሌ ተጠቀሱ እንጂ በኣሁኑ ጊዜ የትግራይ ተወላጅ ሆኖ በኢትዮጵያ ውስጥ በማንኛውም ቦታ ሰብኣዊ ነጻነቱ ተገፎ፤ ለህይወቱና ለንብረቱ ዋስትና ተነፍጎ፤ እንደጠላት እየታደነ የእስር፤ የግድያና፤ የስቃይ ሰለባ እየሆነ ይገኛል።
11. በመገናኛና በማህበራዊ ሜድያ በትግራይ ሕዝብና ማንነት ላይ የተከፈተው ዘመቻም በመሬት በመካሄድ ላይ ካለው ጦርነት የሚበልጥ እንጂ የሚተናነስ ኣይደለም። በከፍተኛ የሃላፊነት ቦታ የሚገኙ የመንግስት፤ የሃይማኖትና፤ የትምህርት ተቋማትና የፖሊቲካ ድርጅቶች መሪዎች የትግራይ ሕዝብ የኢትዮጵያ ጠላት እንደሆነና የችግሮች ሁሉ  መፍትሄም የትግራይ ሕዝብን ከስር መሰረቱ ማጥፋት እንደመፍትሄ ኣድርገው ህዝብን በህዝብ ላይ ለማነሳሳት ያለምንም ሃፍረትና ተጠያቂነት በስፋት የጥላቻ ዘመቻ ማካሄድ ከጀመሩ ከሶስት ዓመታት በላይ አስቆጥሯል።
12. ይህ በትግራይ ህዝብ ላይ የተከፈተው የተቀነባበረ የጥላቻ ዘመቻ ኣደገኛ የሚያደርገው ዘመቻው የሚመራው በጠቅላይ ሚኒስትሩና ከፍተኛ የመንግስት ስልጣን በተቆጣጠሩ ባለስልጣኖች እንዲሁም  እነሱን በሚወክሉ ጋሻ ጃግሬዎችና ኣፈቀላጤዎች በመሆኑ፤ የጥላቻ ቅስቀሳው ወደ ህዝብ እንዲወርድና፤ የተቀሩት የኢትዮጵያ ብሔር ብሔርሰቦችና ሕዝቦችም በትግራይ ሕዝብ ላይ ጦርነት እንዲከፍቱበት የሚያነሳሳ መሆኑን ነው።
13. በዚህ ረገድ በተለይ የተወሰኑ የኣማራ ልሂቃን በትግራይ ሕዝብና ታሪክ ላይ የከፈቱት ዘመቻ ሃላፊነት የጎደለውና ታሪክ ይቅር የማይለው ከመሆኑም በላይ የፖሊቲካና የኢኮኖሚ ኣላማቸውን ለማሳካት ሲሉ የኣማራ ህዝብን በጥላቻ ፖሊቲካ በማደራጀት በትግራይ ሕዝብ ላይ ለከፈቱት ጦርነት የፖሊቲካ፤ የኢኮኖሚና፤ የሰው ሃይል ድጋፍ ማሰባሰቢያ ካደረጉት ውለው ኣድረዋል። ከዚህም የተነሳ ቀላል ነው የማይባል የኣማራ ህብረተሰብ የትግራይ ሕዝብን በጥርጣሬና በጥላቻ የማየትና፤ በትግራይ ህዝብ ላይ በመካሄድ ያለው ጦርነትም ሲደግፍ ቆይቷል።
14. ይህ ኣካሄድ ለኣማራ ህዝብም ሆነ ለኢትዮጵያ የወደፊት ጉዞና ኣቅጣጫ በጣም ኣደገኛና ኣገሪቷ ልትወጣው በማትችለው ቀውስ የሚከታት ኣካሄድ በመሆኑ፤ ይህ እኩይ ተግባርና ኣካሄድ ሁሉም የኢትዮጵያ ብሔር፤ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በኣንድነት ሆነው ሊቃወሙትና በቃ ሊሉት የሚገባ ጉዳይ ነው። ኣንዱን ሕዝብ በሌላው ሕዝብ ላይ በማነሳሳት፤ ህዝብን እንደህዝብ ለማጥፋት የፖሊቲካ ኣላማ ኣድርጎ መነሳት ዘርን ለማጥፋት ለሚደርጉ ዘመቻዎች ዋነኛው ነዳጅ መሆኑ ታውቆ ሁሉም በኣንድነት የጥላቻ ፖሊቲካን መታገልና ለሰላም መስራት ለነገ የማይባል ኣስቸኳይ ጉዳይ ነው።

የኣማራ ህዝብ ሆይ:

የትግራይ ሕዝብ ከኣማራ ሕዝብም ይሁን ከሌሎች የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ተዋልዶና ተጋምዶ የሚኖር፤ ታሪኩንና ባህሉን ከሌላው የኢትዮጵያ ብሄር ብሄርሰቦች ጋር በማስተሳሰር ኢትዮጵያን እንደ ኣገር ለመገንባት ወሳኝ ሚና የተጫወተ ህዝብ ነው። የትግራይ ህዝብ በኢትዮጵያ ረዥም የነጻነት ታሪክ ሂደት የውጭ ወራሪዎችን በመከላከል ረገድ የመጀመሪያውና ዋናው ምሽግ ሆኖ ቆይቷል። ከኣማራም ሆነ ከሌሎች ብሄር ብሄረሰቦች ዘመኑን በሚመጥን ማህበራዊ፤ ኢኮኖሚያውና ፖሊቲካዊ ትስስርን በመፍጠር ኢትዮጵያ እንደ ኣገር ሆና እንድትቆይ የድርሻውን ሲያበረክት ለመቆየቱ ማስረጃዎችን ማጣቀስ የሚያስፈልገው ጉዳይ ኣይደለም። ይህ ሁሉ እንኳንና ለቅርብ ጎረቤት ለሆነው ለኣማራ ህዝብ ቀርቶ ለሌላዉም የኢትዮድያ ህዝብ የተሰወረ ሚስጢር ኣይደለም። ሆኖም በኣሁኑ ወቅት የትግራይ ህዝብ የኣማራ ጠላትና የህልውናውም ዋነኛው ኣደጋ ነው የሚል የጥላቻ መርዝ ተቀብለህ በትግራይ ሕዝብ ላይ በመዝመት "ህልውናህን እንድታረጋግጥ" የሚል ጽንፈኛና በጣም ኣደገኛ ቅስቀሳ እየተነገረህ ይገኛል። ይህ ዓይነቱ መርዝ ህዝብን ከህዝብ በማጋጨት የስልጣን እድሜያቸውን ለማራዘም የሚፈልጉ ሃይሎች የሚነዙት መሆኑን ተገንዝበህ ለእኩይ ተግባራቸው ጆሮ ሳትሰጥ ኢትዮጵያ ኣገራችን ኣሁን ለገጠማት የፓሊቲካ ችግር ከትግራይና ከሌሎች ብሄርና ብሄረሰቦች ጋር ኣንድ ላይ በመቆም እየተካሄደ ያለውን ጦርነት በማስቆም  በሰላምና በወንድማማችነት መንፈስ የሚፈታበትን መንገድ ለመፍጠር የድርሻህን እንድታበረክት ጥሪያችንን እናቀርባለን።

መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ:

ኢትዮጵያ የብሔር ብሔረሰቦች ድምር እንደመሆኗ በትግራይ ሕዝብ ላይ እየደረሰ ያለው የዘር ማጥፋት ጦርነት በሁሉም ላይ የታወጀ መሆኑን ኣውቀህ፤ በትግራይ ህዝብ ላይ የተጣለውን ሁሉም ኣቀፍ ከበባ እንዲነሳና የፖሊቲካ ችግሮች በሰላማዊ መንገድ ብቻ እንዲፈቱ በምትችለው ሁሉ በመንቀሳቀስ ሃገራዊ ግዴታህን የምትወጣበት ጊዜ ኣሁን ነው። ስለሆነም የትግራይ ሕዝብን ለማጥፋት በታወጀው ጦርነት እስካሁን የፈሰሰው ደምና የተከፈለው ይብቃ በማለት በኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት ስም  እየተካሄደ ያለውን የዘር ማጥፋት ጦርነት ኣንዲቆም የዜግነት ግዴታህን ተወጣ። በተለያዩ የኢትዮጵያ ክፍሎች በትግራይ ተወላጆች ላይ ማንነታቸውን መሰረት ባደረገና ምንም ሕጋዊ መሰረት ሳይኖረው እየደረሰ ያለው እስራት፤ መፈናቀል፤ ንብረት መዘረፍ፤ ከስራ መባረር እና የማወከብና የማሳደድ ተግባራት በመቃወም ለፍትህ የምትቆምበት ጊዜ ኣሁን ነው። ይህ ሳይሆን ቀርቶ ኢትዮጵያ እንደኣገር ወደማትቀጥልበት ደረጃ ብትደርስና ብትበታተን፤ ህዝቦች በእርስበርስ ጦርነት ለከፋ ኣደጋና እልቂት ቢዳረጉ ዋናው ተጠያቂዎች ጦርነቱን ያሴሩትና ያወጁት ቢሆኑም፤ መላው የኢትዮድያ ህዝብም ከታሪክ ተወቃሽነት ነጻ እንደማይሆን መታወቅና መገንዘብ ያስፈልጋል። በኣንጻሩ የትግራይ ህዝብ እንደህዝብ በመሬት እንዳይኖርና እንዲጠፋ የዘር ማጥፋት ጦርነት የተሴረበትና የታወጀበት መሆኑን፤ ወደ ጦርነት የገባውም ተገዶና ህልዉናውን ለማስጠበቅ ኣማራጭ መንገድ በማጣቱ ምክንያት መሆኑን በጥልቀት ማወቅና በመገንዘብ ያስፈልጋል።

SJT Executive Board
Email: sjte.info@gmail.com .